# በአንድነት ፓርቲ ዉስጥ ሰሞኑን በተፈጠሩ ክስተቶች ላይ

ግርማ ካሳ (muziky68@yahoo.com)

ሐምሌ 22 ቀን 2001

## በአንድነት ውስጥ የተነሳዉ ዉዝግብ የአንድነትን ጥንካሬን የሚያሳይ ነው!

ሰሞኑን በአንድነት ዉስጥ ተፈጠረ የተባለዉን ውዝግብ በተለይም አፍቃሪ ኢሕአዴግ ድህረ ገጾች ሎተሪ የወጣላቸዉ ይመስል ሲያራግቡትና ሲያሟሙቁት ሰንብተዋል።

ይህ በአንድነት ፓርቲ ዉስጥ የታየው ክስተት በርግጥ የተለየ ክስተት ነው። የተለየ ክስተት የሆነበትም ምክንያት ፓርቲው የተለየ ፓርቲ በመሆኑ ነው። በጥቂት ሰዎች አምባገነንነት የሚመራ እንደ ኢሕአዴግ ባለ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ እንዲህ አይነቱ ክስተት ሊፈጠር አይችልም። በጥቂት ጓደኛሞች በሚስጥር በሚመራ ወይንም ደግሞ አንድ ወይንም ሁለት ሰዎች ብቻ ያሉበት ፓርቲ ውስጥ እንዲህ አይነቱ ችግር አይፈጠርም።

የአንድነት ፓርቲ ጠንካራ፣ በመርህ ላይ የተመሰረቱ ደጋፊዎች ያሉት፣ መሪዎቹን ተጠያቂ የሚያደርግ፣ ከፍተኛ የሆነ ግልጽ የሃሳብ ክርክሮች የሚደረጉበት ድርጅት ነው። በእንደዚህ አይነት ድርጅቶች አለመስማማቶች፣ ክርክሮች ፣ የሃሳብ ግጭቶች ይፈጠራሉ። መሪዎችን ማመስገን እንዳለ ሁሉ መሪዎችን መውቀስና መተቸትም አለ።

በአገራችን መሪዎቻችንን መቃወም አልተለመደም። ብዙ ጊዜ አንድ የፖለቲካ መሪን ወይ ሙሉ ለሙሉ እንቃወመዋለን ወይንም ሙሉ ለሙሉ እንደግፈዋለን። አንድን የፖለቲካ መሪ ከተቃወምን ታማኝ ያልሆንን ተደርጎ ከፓርቲው እንድንወጣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ እንገደዳለን። ይህ መሪዎችን በጭፍን የመከተል፣ ስንቃወማቸው ደግሞ በጭፍን የመጥላት ባህል መስተካከል ያለበት ባህል ይመስለኛል።

በተለይም የአንድነት ፓርቲ ይህንን በኢትዮጵያ ያልተለመደ፣ መሪዎችን ተጠያቂ የሚያደርግ አዲስ የሰለጠነን ፖለቲካ ለመዘርጋት የተነሳ ድርጅት እንደመሆኑ አባላቱ ከአንድነት ፓርቲ ዉስጥ ሳይወጡ መሪዎችን በድፍረት የመጠይቅና የመዉቀሱን ሁኔታ አሁን እንዳየነው ሁሉ ወደፊትም የምናየው እየተደጋገመ የሚመጣ ነገር ነዉ። ስለሆነም ልንደናገጥና ልንፈራ አይገባም።

የአንድነት ፓርቲ አንዱ መርህ ተጠያቂነት ነዉ። መሪዎች ለሚናገሩትም ሆነ ለሚያደርጉት ሁሉ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። የድርጅቱ አባላት መሪዎቻቸዉን ሲቃወሙ ሊበረታታና ሊደገፉም ይገባል። ተቃዉሞ ድርጅትን ያጠነክራል። ተቃዉሞ መሪዎች ውጤት እንዲያሳዩ ይገፋፋል። ተቃውሞ በአንድ ዲሞክራሲያዊ ነኝ በሚል ፓርቲ ዉስጥ ጤናማና ጠቃሚ ነው። አንድ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ነኝ ብሎ መሪዎቹ ተቃዉሞን የሚፈሩ ከሆነ፣ በርግጥ ያ ፓርቲ ችግር አለበት ማለት ይቻላል።

በዚህ አንጻር እንግዲህ በአንድነት የሥራ አስፈጻሚዉ አካል ላይ የቀረቡት ወቀሳዎች፣ ወቀሳዎቹ ጠቃሚ ይሁኑም አይሁኑም፣ በመርህ ደረጃ ሊበረታቱ የሚገባ ናችዉ እላለሁ። በመሪዎቻችን ላይ ተቃዉሞ ማሰማት ካልቻልንማ እንደኛዉን ለምን ኢሕአዴግን እንቀላቀልም ?

እስቲ አስቡት የትኞቹ ፣ በአገር ዉስጥም ሆነ በአገር ቤት ያሉ ድርጅቶች ናቸዉ መሪዎቻቸዉን ፊት ለፊት የሚቃወሙት ? ታዲያ ይህ በአንድነት ዉስጥ የሚታየዉ ክርክር የአንድነት ፓርቲ ጥንካሬን የሚያሳይ አይደለምን ?

## የድርጅቱ ሕግ መከበር አለበት

አንድ ድርጅት የራሱ አሰራርና ደንብ አለው። በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ከጠቅላላ ጉባኤው ቀጥሎ የበላይ አካል የሆነው የላእላይ ምክር ቤቱ ነው። በድርጅቱ ዉስጥ ባሉ መድረኮችም ሆነ በጋዜጦች ላይ አባላት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ። አንዳንዴ በሙሉ ድምጽ ፣ አንዳንዴ ደግሞ የተወሰኑት እየተቃወሙም በድምጽ ብላጫ ዉሳኔዎች ይወሰናሉ። ይህ ሕግና ሥርዓቱን የጠበቀና ዲሞክራሲያዊ የሆነ አሰራር ነዉ።

አባላት የድርጅቱን አመራሮች መቃወም ሙሉ መብታቸዉ የተረጋገጠ እንደሆነውም ሁሉ ከሙብት ጋር የሚመጣ ግዴታም አለ። አባላቱ፣ ሃሳባቸዉ በድምጽ ብልጫ ተቀባይነት ካላገኘ፣ የአብላጫዉን ድምጽ ማክበር ይኖርባቸዋል። አለበለዚያም ዲሞክራሲን ሳይሆን አናርኪንና ዘመነ መሳፍንስትን ነው የምንዘረጋዉ ማለት ነው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምና አንዳንድ የአንድነት ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የፓርቲዉን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን በእጅጉ የሚወቅስ ሁለት ወረቀቶችን በቅርቡ በትነዋል። ከበተኑት ወረቀት እንደተረዳሁት ላእላይ ምክር ቤቱ አንድ ቀን በተሰበሰበ ጊዜ፣ በአንድ አጀንዳ ላይ ዉይይት እንዲደረግ ጥያቄ ቀርቦ ነበር። ይህ ዉይይት እንዲደረግበት የተፈለገዉ አጀንዳ፣ የሥራ አስፈጻሚዉን የሥራ ሂደት ለማሻሻል ከሁለት ሶስት ወራት በፊት በምክር ቤቱ ስብሰባ በተወሰኑ ሃያ ሁለት ነጥቦች ላይ፣ የሥራ አስፈጻሚዉ ምን እያደረገ እንዳለ የሚጠይቅ አጀንዳ ነበር።

የሥራ አስፈጻሚዉ የቀረበዉን አጀንዳ ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍና ዉይይቱ በመድረክ ዙሪያ እንዲደረግ ሃሳብ አቀረበ። የመድረክ ጉዳይ አገራዊ ትኩረትን የሳበና የሌሎች ድርጅቶችን የሚነካ በመሆኑና ለወራት ሲደከምበት የነበረዉ የመድረኩ ማኒፌስቶ በመጠናቀቁ ይመስለኛል፣ የላእላይ ምክር ቤቱ በቅድሚያ በመድረክ ዙሪያ እንዲወያይበት የሥራ አስፈጻሚ የጠየቀዉ።

«የትኛዉ አጀንዳ ይቅደም» በሚል ክርክሮች ተደረጉ። አብዛኛው የላእላይ ምክር ቤት አባል በመድረክ ዙሪያ የዚያን ቀን መወያየትን መረጠ።

እነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም « ...ያለፈዉ ቃለ ጉባኤ ከተነበበ በኋላ በየትም ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅና ሥርዓትን ሁሉ በሚጥስ አሰራር ሎሌዎቻቸዉን አሰልፈዉ በድምጽ ብልጫ ቃለ ጉባኤዉ ዉይይት ተደርጎበት እንዳይጸድቅ አድርገዉ የስብሰባ ደንብንና ሥርዓትን በመሻር ወደሚያንገበግባቸዉ የመድረክ ጉዳያቸዉ ተንደርድረዉ ገቡ። » በማለት ነበር ቅሬታቸዉን ያቀረቡት።

እዚህ ላይ ከላይ እንደጠቀስኩት የነፕሮፌሰር መስፍን ትችት በመርህ ደረጃ የሚደገፍ ቢሆንም የትችታቸዉ ይዘት ላይ ግን ሶስት ችግሮችን አያለሁ።

- እነ ፕሮፌሰር መስፍን በላእላይ ምክር ቤት ዉስጥ በድምጽ ብልጫ እንደተረቱ አልካዱም። ለዚህም ነዉ «በድምጽ ብልጫ» ብለው የጻፉት። በድምጽ ብልጫ የተወሰነን

ዉሳኔ ከመቀበል ዉጭ ሌላ ምን ማድረግ እንደሚቻል ቢነግሩንና ሌላ አማራጮች ካላቸዉ ቢጠቁምን ጥሩ ነበር። ተከራክሮ፣ በድምጽ ብልጫ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ዉሳኔዎች ማሳለፉ ከሥርዓት ዉጭ ከተባለ የቱ ነው ታዲያ ሥርዓትን የተከተለ አካሄድ የሚባለው?

- የላዕላይ ምክር ቤት አባላት፣ ከየክልሉ የተወጣጡ ኢትዮጵያዉያን ያሉበት የጠቅላላ ጉባኤ የመረጣቸዉ ዜጎች ናቸው። የላእላይ ምክር ቤቱ ከጠቅላላ ጉባኤው ቀጥሎ የድርጅቱ የበላይ አካል እንደመሆኑ፣ የላእላይ ምክር ቤት በአብላጫ ድምጽ የሚወስነው ውሳኔ የፓርቲው የመጨረሻ ዉሳኔ ነው። ታዲያ የምክር ቤቱ አባላት እኛ እንደምንፈልገው ድምጻቸውን አለመስጠታቸዉ «ሎሌዎች» ተብለዉ ሊያስጠራቸዉ ይገባልን ? የላእላይ ምክር ቤትን እንደ መሳደብ፣ የሕግ የበላይነትን እንደ መናቅ አድርገዉ ሰዎች ቢወስዱት ተሳሳቱ ማለት ይቻላልን ?

- መድረክ የተለያዩ ድርጅቶችን ለማቀራረብ እየሞከረ ያለ አካል ነዉ። ከዚህ በፊት በተለያዩ መንገድ ይሄዱ የነበሩ ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ ተቀምጠዉ፣ በጋራ አንዲት ኢትዮጵያን ለመገንባት እያደረጉት ያለ ጠቃሚ ምክክር ነው። አሁን ያለው የኢሕአዴግ አገዛዝ አገሪቷን በዘር እየከፋፈለ ባለበት ሁኔታ፣ ከዘር ፖለቲካ አልፎ በመሄድ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር አብሮ ለመሥራታና ለመቀራረብ የሚደረግ ማናችውም ጥረት ሊደነቅና ሊደገፍ የሚገባው ነው እላለሁ።

  የተጎዳነው በዘር በመከፋፈላችን፣ አንዳችን ሌላዉን በጎሪጥ ማየታችን፣ ከሚያቀራርበንና ከሚያገናኘን ይልቅ የሚለያየንናን የሚያጣላንን መፈለጋችን፣ አንዳንች በአንዳችን ላይ የጥራጣሬ መንፈስን ማሳደራችን .. ነዉ። በአሁን ጊዜ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ጨለምተኝነትን የሚያስወግድ ልጆችዋን የሚያቀራርብ በጎ እንቅስቃሴ ነው።

  ታዲያ የአንድነት ፓርቲ በመድረክ ዉስጥ ኢትዮጵያዉያንን ለማቀራረብ የሚያደርገዉን ጠቃሚ ሂደት «ወደ ሚያንገበግባቸዉ የመድረክ ጉዳያቸው» በማላት ማጥላላት ተገቢ ነዉን ? ከመድረክ ጋር የአንድነት ፓርቲ መሥራት የሚችልበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ለሥራ አስፈጻሚው ዉክልና የሰጠዉ የላእላይ ምክር ቤቱ አይደለምን ? በመድረክ ማኒፌስቶ ውስጥ መሻሻል ያለባቸዉ እንዲሻሻሉ፣ በጎሳ ላይ ብቻ ሳይሆን ጂኦግራፊን፣ ኢኮኖሚና የሕዝብ ፍላጎትንና ሌሎች ጠቃሚ መስፈርቶችን ከግምት ዉስጥ ያስገባ ፌደራል አወቃቀርን የመሰሰሉትን  ቁልፍ የአንድነት እሴቶችን መድረኩ እንዲቀበል ማሳመንና መገፋፋት፣ ስህተት ተሰራ ከተባለ ደግሞ ለማረም መጣር ይገባል እንጂ አገርን ሊጠቅም የሚችልን አካል የኛ ጉዳይ እንዳልሆነ በመቁጠር «ጉዳያቸው» ይባላልን ?

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ሃሳባቸዉን ለመግለጽ የማይፈሩ፣ መንግስቱ ኃይለማሪያምን ከስልጣን ውረድ ያሉ ቆራጥ የዲሞክራሲ አባት ናቸዉ። ነገር ግን ሰዉ ናቸዉና እርሳቸዉም የሚሳሳቱበት ጊዜ ይኖራል።

ከላይ እንደጠቀስኩት የሥራ አስፈጻሚውን መውቀሳቸዉና መተቸታቸው  በመርህ ደረጃ የሚደገፍ ቢሆንም ሰሞኑን በበተኑት ሚዛን የማይደፋ ወረቀት ግን እርሳቸዉና አብረዋቸዉ ያሉት ወገኖች መሳሳታቸዉን በአክብሮት ለመግለጽ እወዳለሁ። ማንም የተበተኑትን ወረቀቶች ያነበበ ሰው፣ ወረቀቶቹ ጸሃፊዎቹን እራሳቸዉ የሚያስገምቱ እንደሆነ ይረዳል ብዬ አስባለሁ።

ከስህተቶቻችን ተምረን ፣ በግለሰቦች ላይ «እንዲህ አደረገ ፣ እንዲህ አደረገች» የሚሉ ተራ አሉባላታዎችን አቁመን፣ መስተከከል አለበት ለምንላቸዉ አጀንዳዎች በሰለጠነና የድርጅቱን ሕገ ደንብ በጠበቀ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ መዘጋጀት ያለብን ይመስለኛል። ተቃዉሟችን አስፈላጊ ነዉና እንቀጥልበት። ነገር ግን የድርጅቱን ሕግና ሥርዓት በማክበርና በፍቅር እናድርገዉ። የሰዉ ስም እየጠራን መሳደባችንን እናቁምና የምንጠቀማቸዉን ቃላቶች እየመረጥን በመከባበር እንወቃቀስ።

## አጭር መልእክት ለአንድነት አመራር አባላት

ይህን ብዬ ለአንድነት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አጭር መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ። በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ የሚደግፈዉ ፓርቲ አመራር አባላት ናችሁ። ሰሞኑን አንዳንዶቻቹህ በግለሰብ ደረጃ ብዙ ዉርዥብኝ እንደደረሰባቹህ አንብቢያለሁ። ልታዝኑና ልትጎዱ እንደምትችሉም ይገባኛል።

የዚያኑ ያህል ደግሞ ብዙ ስህተቶች እንደሰራቹህና የቀረበባቹህ አንዳንድ ወቀሳዎችም መሰረት ያላቸዉ እንደሆኑ እናንተም የምታጡት አይመስለኝም።

ስለዚህ የቀረቡትን ቅሬታዎች በቅንነትና በትህትሃ ተቀብላችሁ፣ አሁን የሚደግፏቹህ የበለጠ እንዲደግፏችሁ፣ የሚቃወሟችሁ ደግሞ ከመቃወም ወደ ድጋፍ ሰጪነት እንዲመለሱ የማድረግ ተጨባጭ ሥራ መስራት አለባችሁ እላለሁ። መሪ ማለት የሚቃወሙትን የሚያስወግድ ሳይሆን የሚቃወሙትን አሳምኖ ወደ ትግሉ ጎራ መልሶ የሚያመጣ ነዉ ። መሪ ማለት «እኔ ለምን ተነካዉ» ብሎ በእልህ የሚንቀሳቀስ ሳይሆን ረጋ ብሎ የአገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚያስጠብቅ ማለት ነዉ። እንግዲህ ይህን አይነት በሳል አመራር አሳይታችሁን እንደምታኮረን ትልቅ ተስፋ አለኝ።